# አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ስጦታ ተበረከተላቸው

<u>ለገጣፎ፣ ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም</u>  የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከአዋሽ ባንክ ጋር በመሆን ለአቶ ቡልቻ ደመቅሳ ሥጦታ አበርከተላቸው።

ለገጣፎ በሚገኘው የአቶ ቡልቻ መኖሪያ ቤት በመገኘት ሥጦታውን የሠጡት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ እና የአዋሽ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ፀሐይ ሽፈራው ናቸው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለአቶ ቡልቻ በቅርስነት የሚያዝ የልዩ ታሪካዊ ሁነቶች ማስታወሻ የወርቅ ሳንቲም የሸለማቸው ሲሆን፣ ለእርሳቸውና ለባለቤታቸው ወይዘሮ ሔለን ገብረእግዚአብሔር ካባ አልብሷቸዋል።

የአዋሽ ባንክ ደግሞ ደግሞ የምሥጋና የምስክር ወረቀትና የወርቅ ሜዳሊያ አበርክቶላቸዋል።

የ91 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑት አቶ ቡልቻ  ስጦታው የተበረከተላቸው ለሀገራቸው ፋይናንስ ዘርፍ ላበረከቱላት የረዥም ዘመን አገልግሎት ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር ይናገር ደሴ በፋይናንስ ዘርፍ አስተዋጽኦ ካበረከቱት ኢትዮጵያውያን መካከል አቶ ቡልቻ በቀዳሚነት የሚጠቀሱ አርአያ ግለሰብ በመሆናቸው የሚመሰገኑ መሆናቸውን በሥነሥዓቱ ላይ ተናግረዋል።

አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በቀዳማዊኃይለሥላሴ  ዘመነ መንግሥት ከ1959 ዓ.ም. ጀምሮ የደርግ መንግሥት ሥልጣን እስኪያዘበት ድረስ የገንዘብ ምክትል ሚኒስትር በመሆን ማልገላቸው ይታወቃል። በተጨማሪም ኢትዮጵያን ወክለውን በዓለም ባንክ ውስጥ የቦርድ አባል ሆነው ሰርተዋል።

በደርግ ዘመነ መንግሥት ወቅትም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሥር የናይጀሪያ ቅርንጫፍ ውስጥ ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል።

ወደ አገራቸው በመመለስም በፋይናንስ ዘርፍ አስተዋጽኦ ያበረከቱት አቶ ቡልቻ በተለይ ከአዋሽ ባንክ መሥራቾች አንዱ በመሆን በግል የባንክ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ፈር ቀዳጅ መሆናቸውም ይታወቃል።

አዋሽ ባንክ ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ መሠረት በመጣል የአቶ ቡልቻ አስተዋጽኦ የላቀ መሆኑን የአዋሽ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ጸሐይ ሽፈራው በሥነሥርዓቱ ላይ ተናግረዋል።

አቶ ቡልቻ ለተበረከተላቸው ሥጦታና ዕውቅና ምሥጋናቸውን አቅርበዋል።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስና በሕግ ዲግሪዎች የተመረቁት አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በ54 የትዳር ዘመናቸው 6 ልጆችን አፍርተዋል።

ሐሙስ ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተካሄደው ሥነሥርዓት ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ፍቃዱ ድጋፌ፣ አቶ ሰሎሞን ደስታና አቶ እዮብ ገብረየሱስ፣ እንዲሁም የለውጥ ማኔጅመንት፣ ዕቅድና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አባተ ምትኩ ተገኝተዋል።